# ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2018 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ የተሻለ ዝናብ የሚገኝበት ጊዜ ነው፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ ክስተቶች በአብዛኛው የሀገረቷ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው በመቀጠላቸው ምክንያት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን የሸፈነ ዝናብ አግኝተዋል። በመሆኑም በሰሜን ምስራቅ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፤ የደቡብ፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና የምስራቅ የሀሪቱ አካባቢዎችም አልፎ አልፎ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸው፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት ትግራይ፤ አማራ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ ከኦሮሚያ የወለጋ፣ የኢሉአባቦራ፣ የጂማ፣ የአርሲና ባሌ፣ ጥቂት የጉጂና የቦረና እንዲሁም የሸዋ ዞኖች፤ ድሬዳዋና አንዳንድ የምዕራብና የምስራቅ ሐረርጌ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋ፣ የሸካ፣ የቤንች ማጂ፣ የስልጤ፣ የጉራጌ፣ የጋሙጎፋ፣ የሀዲያና ከምባታ፣ የወላይታ፣ የሲዳማና የጌዶ ዞኖች፤ አብዛኛዎቹ የአፋር ክልል ዞኖች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው።

በአሥሩ ቀናት ውስጥ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በስሪንቃ 124.0፣ በአዲስ አበባ 54.4፣ በአልጌ 44.0፣ በአርጆ 55.7፣ በአምባ ማርያም 49.6፣ በበደሌ 45.3፣ በቡኢ 41.8፣ በቻግኒ 64.1፣ በገዋኔ 46.6፣ በጊምቢ 57.4ና 49.5፣ በላሊበላ 44.5፣ በመተማ 42.8፣ በሞጣ 53.2፣ በመካነሰላም 65.3፣ በማይፀምሪ 60.4፣ በነጆ 55.7፣ በፓዌ 60.4፣ በሻውራ 62.5፣ በሲርባ ኣባያ 66.2ና 46.2፣ በአክሱም 49.6፣ በአማን 63.3፣ በጉንዶ መስቀል 64.7፣ በአምደወርቅ 48.3፣ በአዲስ አበባ ቦሌ ኢንጂነሪንግ 69.4፣ በከማሽ 64.3 እንዲሁም በሶጌ 58.8 እና በሌሎች በአንዳንድ ስፍራዎችም ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ ዝናብ እንደተመዘገበ ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል። ይህም ሁኔታ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለወንዞች ሙላትና ለቅፅበታዊ ጎርፍ መከሰት ምክንያት እንደነበረ ከተመዘገቡ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የነበረው ዝናብ ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ትግራይ፤ አማራ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ አብዛኛው ኦሮሚያና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከዞን 1 በስተቀር ሁሉም የአፋር ዞኖች እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ ከ25-186 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ2-10 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ትግራይ፤ አፋር፤ አብዛኛው አማራ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ከጋምቤላ ዞን 1 እና 2፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ቤንች ማጂ፤ ከፊቸሸክቾ፣ ጉራጌና ሀዲያ እና የሲዳማና የጌዶ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ጂማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖችና አዲስ አበባ እንዲሁም ጥቂት የአርሲ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



## ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





በወቅቱ ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች | ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና የስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

በኦገስት ሁለተኛው አስር ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ የሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ የመኸር ሰብል አብቃይና የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ የተጠናከረ ዝናብ ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለጓሮ አትክልት፣ ለዕፅዋት ልምላሜ፣ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት መሟላት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ በምዕራብ ፣ በደቡብ ምእራብ፣ በመካከለኛው፣ እንዲሁም በሰሜን የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ከባድ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ ቅጽበታዊ ጎርፍ በተወሰኑ ቦታዎች በመከሰቱ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰብሎች ፣ በአፈር ጥበቃ ሥራ እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ ፣ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ በአንጻሩ ባለፉት አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ቀደም ባሉት ቀናት የእርጥበት እጥረት ለነበረባቸው በቆላማ አካባቢዎች ለሚኖሩት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ

# በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 11-20 ኦገስት 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽና በሰሜን ዋና ዋና ተፋሰሶች እንዲሁም የመካከለኛው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ተፋሰሶች፣ አብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ የላይኛው አፋርደናከል፣ ስምጥ ሸለቆና ኦሞጊቤ እና የመካከለኛውና የላይኛው አዋሽ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም የታችኛው ባሮአኮቦ፣ የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው አፋርደናከል ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ላይ የቆዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ባለፉት አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ለውሃ ሃብት ከፍተኛ ግብዓት ከመሆኑም በላይ በመጠንና ስርጭት ረገድ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በተከታታይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች እና የውሃ ማጠራቀሚያዎች ከመደበኛው ወቅት ቀደም ብሎ የውሃ ሙላት ተከስቷል፡፡ የተቀሩት የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ተስተዉሎባቸዋል (ካርታ 5)።

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## <u>እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2018 የሚኖረው</u>
## <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት በመጨረሻዉ አስራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት የሚኖራቸው ሲሆን፤ ቀስ በቀስ ወቅታዊው ዝናብ ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ ስፍራዎች ላይ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ጥንካሬ በአብዛኛው የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም በምዕራብ አጋማሽ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም በፀሐይ ሀይል ታግዞ ከሚፈጠረው ጠንካራ የሆነ የደመና ክምችት ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶና ነጎድጓድ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይጠበቃል፡፡

<u>በአጠቃላይ በሚቀጠሉት አስራ አንድ ቀናት የትግራይ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ እና ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋ እና የሸዋ፣ ዞኖች፣ ጂማ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲና ባሌ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሀድያ፣ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ፣ ሲዳማ እና ጌዲዮ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆንና አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊከሰት እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ አፋር፤ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ እና ሲቲ ዞኖች እንዲሁም ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሰገን ህዝቦች መደበኛና በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡</u>

## <u>እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>
## <u>በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የኦገስት ቀጣይ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር አብቃይና የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው አሁን ባለው ጥንካሬ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም አልፎ በአንዳንድ አካባቢዎች በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለይም መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ከላይ በትንበያ በተጠቀሱት ዞኖች እያከናወኑ ላሉት የመኸር እርሻ አንቅስቃሴ የሚጠበቀው የተጠናከረ እርጥበት ገንቢ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም

በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችና ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር የሚጠበቀው እርጥበት ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ይጠበቃል፡፡ ሆኖም ከእርጥበት መብዛት ጋር በተያያዘ የአረም መስፋፋትና የሰብሎች በሽታ መከሰት ሊገጥም ስለሚችል አስፈላጊውን ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ከባድ ዝናብ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በሰብሎችም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ አስቀድሞ ማከናወን ይመከራል፡፡ በአንፃሩ መደበኛና ከመደበኛ በታች የሆነ እርጥበት እንደሚኖራቸው በትንበያው የተጠቀሱ አካባቢዎች የተገኘውን እርጥበት በአግባቡ መያዝ፣ የዝናብ ውሃን መሰብሰብና ማጠራቀም የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ማለትም እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2018 በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚያገኙበት ወቅት ቢሆንም፤ ቀስ በቀስ በሰሜን ምስራቃዊው የሀገሪቱ ክፍል ከሚገኙ ተፋሰሶች የዝናብ መጠን እየቀነሰ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃችን ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት የአየር ሁኔታው በዉሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊኖር የሚችለውን ተፅዕኖ ስንመለከት የተከዜ፣ የባሮ አኮቦ፣ አብዛኛው የአባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ስምጥ ሸለቆና አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሆነ ጎርፍ ሊከሰት እንደሚችል ትንበያችን ያመለክታል፡፡ በተለይም ከዚህ በፊት በነበረው የአየር ሁኔት መሬቱ ውሃ የጠገበ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚዘንበው ዝናብ ወደ ወንዞች ስለሚገባ የወንዞች ሙላት ሊጋጥም ይችላል፡፡ ይህም ሁኔታ ጎርፍ ሊያስከስት ስለሚችል በወንዞች ዳርቻና ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ የሚኖረው ማህበረሰብና የሚመለከተው አካል ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ እናሳስባለን፡፡ በተጨማሪም የታችኛው አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ መካከለኛው ዋቢሸበሌና የላይኛው ኦጋደን ተፋሰሶች ከመደበኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን ሊያገኙ የሚችሉ ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ከፍተኛ ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል መረጃዎች የመላክታሉ በመሆኑ ዝቅተኛ አካባቢዎች ላይ የሚኖረው ማህበረሰብ ጥንቃቄ ማድረግ እንደለበት እናሳስባል፡፡